**Advanced Journal of Interdisciplinary Studies**
**Volume 10, Issue 1, 2026 | Pages 2976–2987**
Journal homepage: www.ajids.dmu.edu.et

*Research Article*

# ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን ከሚያረክሱ ሁነቶች የሚያነጹ ሥርዓቶች ትንተና በባሶሊበን ማኅበረሰብ ማሳያነት

# An analysis of Rituals that purify socio-cultural values from practices that Impure them, as demonstrated by the Basoliben community

ሙሉቀን የኔሰው ጥሩነህ[1]፣ ለማ ንጋቱ[2]፣ ዋልተንጉሥ መኮንን[1]

*[1] ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል፤ ሂዩማኒቲ ፋኩሊቲ፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ፖ.ሳ.ቁ. 79፣ ባህርዳር፣ ኢትዮጵያ*
*[2] የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል፤ ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ፖ.ሳ.ቁ. 378፣ ጅማ፣ ኢትዪጵያ*

**ARTICLE INFO**

Received: 10 November 2025
Revised: 10 June 2026
Accepted: 01 September 2026
Available online: 15 September 2026

**KEYWORDS/ቁልፍ ቃላት**

*Social values/ማኅበራዊ እሴት፣*
*Impurity/ርኩሰት፣*
*Purification/መንጻት፣*
*Basoliben/ባሶሊበን*

**አህጽሮተ ጽሁፍ/ABSTRACT**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባሶሊበን ማኅበረሰብ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን ከሚያረክሱ ተግባራት የሚያነጹ ልማዳዊ ስርዓቶችን ተንትኖ ማሳየት ነው። ጥናቱ ዓይነታዊ የኢትኖግራፊክ የአጠናን ዘዴን ተከትሎ የተጠና ሲሆን፣ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለ መጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይትና በምልከታ ነው። የተሰበሰቡት መረጃዎች በመዋቅራዊ-ተግባራዊ ንድፍ ሐሳብ፣ የመንጻትና መርከስ ቲዎሪ/purification-defilment/impurity theory/ እና በሞራላዊ ፍልስፍና ንድፍ ሐሳብ በመጠቀም በጭብጣዊ የትንተና ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። በጥናቱ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት በዓላማ ተኮርና ቅብብሎሽ የወሳኝ ናሙና አወሳሰድ ስልቶች በመጠቀም ነው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የባሶሊበን ማኅበረሰብ ርኩሰት የሚላቸውን ተግባራትና ክስተቶች የሚያነጻባቸው እሴቶች ከኃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሥርዓቶችና ደንቦች ጋር የተሳሰሩ መሆናቸው በጥናቱ ተገልጿል። በመሆኑም እነዚህ ስርዓቶች በዋናነት ከሞራልና ከጤና ጋር የተያያዙ የርኩሰት ክስተቶችንና ተግባራትን ለማስጠበቅ የሚረዱ ሲሆን፤ የግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ማንነት ከሚያዛባ ሁነት ለመጠበቅ፤ ከሚያስገልሉ ተግባራት በመመለስ ማኅበራዊ ተቀባይነት ለማስገኘት፣ የዕርስ በዕርስ ትስስርን ለማጠናከር ይረዳሉ። በጥቅሉ ማኅበረሰበቹ ሕይወታቸውን ከሚያናጉ፣ ማኅበራዊ ትስስራቸውን ከሚያበላሹ፤ ጤናቸውን ከሚነሱ፣ ተግባራት ለመንጻት ሥርዓቶች አስፈላጊ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በመሆኑም ማኅበረ-ባህላዊ የማንጻት ሥርዓቶች ሰዎች ሕይወታቸውን ከሚያበላሹ ተግባራት ለመመለስ የሚረዱ መሆናቸውን ጥናቱ ይገልጻል።

The main objective of this study is to investigate and demonstrate the socio-cultural value based on purification rituals from Defiling or Impurity on the Basoliben community. The study was conducted following a qualitative type of ethnographic research method, and field data were collected through interviews, focus group discussions, and observation. The gathered data were analyzed by a thematic analysis framed by structural-functional approach, purification-defilement/impurity theory, and Moral Foundation theory. And also the informants were selected by purposive and snowball sampling techniques. The finding of the study indicate that, for the Basoliben community, one of the mechanisms used to purify what is considered defilement taboos are linked to religious and social values. The Basoliben community considers values and rituals that purity and Impurity taboos are linked to

*Corresponding author: mulukenyenesew@gmail.com (ጥሩነህ ሙ.የ.)*

DOI: http://doi.org/10.20372/ajids.2026.2977

religious and social norms. Therefore, these values help to protect against defile events and practices related to morality and haygine; protect individuals and groups from polluting their identities; to gain social acceptance by refraining from discriminatory practices; and strengthen interpersonal relationships. Generally; the results of the study indicate that values are essential for societies to purify disrupt their lives, pollution of their social bonds, and harm their hygiene. Therefore, the socio-cultural systems help people restore from practices that disrupt their norms.

## 1. መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ማኅበራዊ እሴቶች አንድ ማኅበረሰብ እንዴት መኖር እንዳለበት የሚወስኑ መመሪያዎች ሲሆኑ፣ የመንጻትና መርከስ ጽንሰ-ሐሳቦች እነዚህን የእሴት ደንቦች በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ርኩሰት እና መንጻት ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባውን እና ሊያደርጉት የማይገባውን በመለየት፣ የማኅበራዊ ባህርይን ይቆጣጠራሉ (Bogaert, 2025 and Douglas, 2002)። ደንቦችን መጣስ እንደ ርኩሰት ሊቆጠርና ማኅበራዊ ቅጣትን ሊያስከትል ይችላል። የመንጻት ሥርዓቶች ደግሞ፣ የተጣሱ ደንቦችን ለማስተካከል እና ማኅበራዊ ደንብን ለመመለስ የሚያስችሉ መንገዶችን ያቀርባሉ። Aspen (2001) የመንፈስ ባለቤቶች (spirit mediums) የሚያቀርቧቸው የመንጻት ሥርዓቶች፣ አንዳንድ ጊዜ ማኅበራዊ ደንቦችን በመጣስ የተከሰቱ ችግሮችን ለመፍታትና ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ እንደሚረዱ ያብራራሉ።

የንጽሕና እና የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳቦች በቀጥታ ከእነዚህ እሴቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው። Douglas (2002) Radcliffe-Brown (1952) ን ጠቅሰው ንጹሕ ተብሎ የሚታሰበው ነገር የማኅበረሰቡን አዎንታዊ እሴቶች የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ርኩስ ተብሎ የሚታሰበው ደግሞ በእሴቶቹ ላይ ስጋት የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል። የማንጻት ሥርዓቶች ደግሞ እነዚህን ባህላዊ እሴቶች ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳሉ። Fardon (2016) እና Feder (2021፣ 7-8) ርኩሰት በሃይማኖታዊም ሆነ በባህላዊ እሳቤዎች (ተፈጥሯዊም ቢሆኑ) በአካል ለቆሸሹ ነገሮች ወይም ሰዎች መጠሪያ መሆኑን ሲገልጹ Bogaert (2025) እና Blidstein (2017, 9) በበኩላቸው ርኩሰት አካላዊ ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ስነልቡናዊ ስሜት፣ ሞራላዊና ማኅበራዊ ደረጃ የሚገልጽ መሆኑን ያስረዳሉ። በመሆኑም፣ ርኩሰት አንድ ማኅበረሰብ በእምነትም ሆነ ባህላዊ ሥርዓት (ተፈጥሯዊም ቢሆን) በማይፈቀዱ ሁኔቶች ውስጥ መሳተፍ የሚያስከትለው የተግባር ውጤት መሆኑን ነው። Lockett (2008፣ 29) ርኩሰት ከኃጢያት/sin ተግባር ጋር እንደሚያያዝ እና ያልተፈቀዱ ድርጊቶችን ከመፈጸም ጋር እንደሚገናኝ ገልጸዋል። በሌላ በኩል Feder (2016፣ 100) ደግሞ ርኩሰት የሰዎች እምነት /belief/ የሆነና ንጹህ ባልሆኑ ወይም አደገኛ በሆኑ ቁሶች ንክኪ ምክንያት የሚከሰት የህመም ዓይነት ነው ይላሉ። ሃሳቦች እንደሚያሳዩት በማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ የሰዎችን ጤና የሚያውኩ ህመሞችና የደንብ ጥሰቶች ከሰዎች ያልተፈቀዱ ተግባራት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ነው። Duschinsky (2016); Lampitt (2012) ን ጠቅሰው ደግሞ ሃይማኖታዊ ደንቦች የሰዎችን ሞራላዊ እሴቶች በመቅረጽ የማኅበረሰብን የማንነት ስሜት በመትከል በተከታዮቹ መካከል የጋራ እምነቶችን እና እሴቶችን ያጠናክራሉ ይላሉ።

የጥናቱ ትኩረትም በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ በሆነው በባሶሊበን ማኅበረሰብ ላይ ነው። ‹‹ባሶሊበን›› ወረዳ የምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ ከሆነችው ደብረ ማርቆስ በስተ ደቡብ 27 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በምስራቅ አዋባልና አነዳድ ወረዳ በምዕራብና ሰሜን ጎዛምን ወረዳ በደቡብ ምስራቅና በደቡብ ምዕራብ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ይዋሰናል (የባሶ ሊበን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት፣ 2009)። በመሆኑም፣ ይህ ጥናት ማኅበረ-ባህላዊ እሴትን ከሚያረክሱ ተግባራትና ክስተቶች የሚያነጹ ሥርዓቶችን መርምሯል።

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ክፍተትን ለመሙላት ያለመ ነው። በኢትዮጵያ በባህል ጥናትም ሆነ በሌሎች የትምህርት ዘርፎች፣ ማኅበረ-ባህላዊ የንጽሕና መገለጫ እሴትን የሚያሳዩ ጥናቶች ቢኖሩም የሚያረክሱ ተግባራት ከማንጻት ሥርዓቶች ጋር ተገናዝበው አልተጠኑም። በማሳያነትም፦ ከነውር ጋር በተያያዘ ሞላ ጀንበሬ (2009) ‹‹የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት›› በሚል ርዕስ ባጠኑት ጥናት፤ አያል ዋሴ(2011) የነውር እሳቤ ከልማዳዊ ህግ አንጻር ባጠኗቸው ጥናቶች ነውር በሚል ያቀረቧቸው መረጃዎች ከመርከስ ጋር የተያያዙ መሆኑን በጨረፍታ ገልጸዋል። ይሁንና ከመርከስ ተግባር የሚያነጹ ሥርዓቶችን አላሳዩም። በሌላ መንገድ Antohin (2014) ‹‹Expressions Of Sacred Promise:

Ritualand Devotion In Ethiopian Orthodox Praxis›› በሚል ርዕስ በሰነሰብ መስክ ያጠኑት ጥናት በኢኦተቤ[1] አምልኳዊ ሥነሥርዓቶች የአምላክን ትዕዛዝ መጣስ የኃጢያት ተግባር ማሳያ ስለመሆኑ ጠቁመዋል። በዚህ ጥናት ኃይማኖታዊ ህግን ማክበር የንጽሕና፣ ኃጢያት ደግሞ የርኩሰት ተግባር መገለጫ መሆኑን ቢጠቁሙም ባህላዊ የማንጻት ሥርዓትን አላካተቱም። በተጨማሪም በልስቲ (2011) ‹‹ደም አድርቅ የግጭት አፈታት ስርዓት በባሶ ሊበን ወረዳ›› በሚል ርዕስ ባጠኑት ጥናት የእርቅ ሥርዓቱን ሲገልጹ ደምን በደም የማድረቅ ሥርዓትን ቂምና ጥላቻን መተው መሆኑን አሳይተዋል። ነገርግን ከእርቅ ሥርዓት አውድ ባለፈ በሌሎችም የማንጻት አውዶች ከበሽታ፣ ከተፈጥሯዊ አደጋዎች ለመንጻትና ሞራላዊ ንጽሕናን ማስጠበቂያ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶች አልተመረመሩም።

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ማኅበረሰብ የርኩሰት ተግባራት ብሎ የሚያምንባቸውን ሁነቶች ለማንጻት የሚረዱ ሥርዓቶች በጥልቀት አልመረመሩም፤ በማንጻትና ርኩሰት ቲዎሪና ጽንስ ሐሰቦችም ተገናዝበው አልተጠኑም። ስለሆነም ከጽንስ ሃሳብ ልዩነት በለፈ የቲዎሪ እና የስነዘዴ ልዩነቶች አሉ። ይህ ጥናት እነዚህን አካዳሚያዊ ክፍተቶች ለመሙላትና በጽንሰ-ሐሳቡ ዙሪያ ጥልቅ ግንዘቤ ለመስጠት ያለመ ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ(ዎች)

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በባሶሊበን ማኅበረሰብ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን የሚያረክሱ ተግባራትና የማንጻት ሥርዓቶችን መመርመርና መተንተን ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፡- ከርኩሰት ተግባራት የሚያነጹ ልማዳዊ ሥርዓቶችን መለየት፤ የሚያነጹ ሥርዓቶች ከምን ከምን የመርከስ ሁነቶች እንደሚያነጹ መተንተን፤ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

1. ተጠኚው ማኅበረሰብ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ማኅበራዊ ደንቦችና እሴቶች በጽሑፍ እንዲሰነዱ፤ የማኅበረሰቡ ባህላዊ ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል።
2. በሌላ መንገድ ደግሞ በማኅበረ-ባህላዊ እሴቶች ላይ የሚከሰቱ የርኩሰት ተግባራትን በማስረዳት፤ የማኅበረሰቡን የክልከላ አውዶች እንዲሁም ማንነታቸውን የሚያስጠብቁ የንጽሕና እሳቤዎች በማኅበረሰቡ ፍልስፍና በመመስረት መጠናቱ ለሌሎች ለተለያዩ ሙያተኞች መነሻ ዕውቀት ይሆናል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር የተገደበ ነው። ከቦታ አንጻር፡- በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል በባሶሊበን ማኅበረሰብ ላይ አተኩሯል። ይህ ቦታ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ ከዚህ በፊት ከነበራት የመስክ ልምድ አንጻር ልማዳዊ እሴቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን መመልከቷ ነው። ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር፡-ከርኩሰት ሁነቶች የሚያነጹ ማኅበራዊና ኃይማኖታዊ እሴቶችን መተንተን ላይ ተወስኗል።

# 2. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ (Research Methodology)

ይኸ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር አካሄድን የተከተለ ሲሆን፣ በተለይም ክስተቶችን በተፈጥሯዊ ከባቢአቸው በጥልቀት ለመረዳት በሚያስችለው የኢትኖግራፊ የምርምር ንድፍ ላይ አተኩሯል። ጥናቱ የተመራው በተርጓሚ (Interpretive) የምርምር አተያይ ሲሆን፣ ይኸም ክስተቶችን በማኅበረ-ባህላዊ እውቀት ላይ ተመስርቶ ለመተንተንና ትርጉም ለመስጠት ያለመ ነው።

## 2.1. የናሙና አመራረጥ ስልት

የጥናቱ አካባቢ እና ለትንተናው የሚሆኑ መረጃዎች በዓላማ ተኮር ናሙና የተመረጡ ሲሆን፣ የመረጃ ሰጪዎች ደግሞ ጉዳዩን በቅርበት ያውቃሉ ተብለው የሚታመኑ የማኅበረሰቡ አባላትን በጥቆማ ለመለየት በሚያስችለው አመልካች/ቅብብሎሽ (Snowball) ናሙና ተለይተዋል። በዚህም የጾታ፣ የትምህርት ደረጃ እና የእድሜ ልዩነቶችን ያካተተ ተዋፅኦ ነበረው። ከወረዳውም ለመረጃው አመቺነት አምስት ቀበሌዎች[2] ተመርጠዋል።

[1] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

[2] ልምጭም፣ የጁቤ 01 ቀበሌ፣ ደን፣ ኮርክና የላምገንጅ

### 2.2. የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች

የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ነው። በምልከታ ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ተካሂዷል። በተሳትፏዊ ምልከታ የማንጫ እሴቶችን ለመመርመር የተለያዩ አውዶች ጥቅም ላይ ውለዋል። በመሆኑም በሠርግ ጋብቻ፣ በአራስ ቤት፣ በግብርና ስራዎች፣ በሽታን ለመስወገድ በሚፈጸመው ግስ ሥርዓት፣ በኃይማኖታዊ ጠበል፣ በልማዳዊ ጠበል አውዶች (ከኃይማኖታዊ ጠበል ውጪ ማኅበረሰቡ ለጤናና ለበረከት ማስጠበቂያነት ጠበል በሚል የሚያምኑባቸውን ባህላዊ ጠበሎች) ላይ በመሳተፍ ሰዎች ጤንነትንና፣ በረከትን ለማስጠበቅ የሚጠቀሙባቸውን እሴቶች ለመሰብሰብ ተችሏል። በሌላ መንገድ የአጥኚዋን ቀጥተኛ ተሳትፎ የማይጠይቁ መረጃዎችን ከዳር ቆሞ በመመልከት ለመሰብሰብ ተችሏል። በቃለመጠይቅ ዘዴ ደግሞ ጥልቅ ቃለመጠይቅ (In-Depth Interviews) ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ርኩሰት የሚያስከትሉ ተግባራትና መገለጫቸው ምን እንደሆነ (የደም መቃባት ቁምና ጥላቻ፣ በረከት የሚያሳጡ ክስተቶች፣ ጤንነት የሚጋፉ በሽታዎችና የበረድ አደጋዎች)፣ ርኩሰትን ከማኅበረሰቡ እሴት አንጻር በምን በምን መንገዶች እንደሚያነጹ፣ የሚያነጹ ሥርዓቶች ከምን ከምን ተግባራት ለመንጻት እንደሚረዱ ከሽማግሌዎች፣ ከኃይማኖት አባቶች፣ ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በማኅበረሰቡ አውድ ተሰብስቧል። በቡድን ውይይት ደግሞ ሦስት ቡድን ውይይት በመጠቀም በእያንዳንዱ ቡድን ስድስት ሰዎችን በማሳተፍ መረጃዎችን ከማጠናከር ባለፈ ለማመሳከርም (to triangulat) ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በጭብጣዊ ትንተና (Thematic analysis) ዘዴ ተተንትነዋል። የመረጃ አተናተን (አደረጃጀት) ሂደቱም በተለያዩ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን (በማስታዎሻ ደብተርና በመቅረጸ ድምጽ የተያዙትን መረጃዎች) ማሰባሰብና ወደ ጽሑፍ ትራንስክራይብ ማድረግ፤ ወደ ጽሑፍ የሰፈሩ መረጃዎችን በይዘታቸው ባላቸው ተዛምዶ በየጭብጣቸው በማደራጀት ተተንትነው ቀርበዋል። ከጥናቱ ሥነምግባር አንጻርም የመረጃ ሰጪዎችን ስማቸውን በኮድ በመጥቀስ በጽሑፉ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

### 2.3. የንድፍ ሐሳብ ማሕቀፍ (Theoretical framework)

ይኽ ጥናት በሞራላዊ ፍልስፍና/ስነምግባራዊ መሰረቶች፣ በመዋቅራዊ-ተግባራዊ እና በመንጻትና መርከስ ንድፍ ሐሳቦች በመጠቀም መረጃዎች ተተንትነዋል። ሞራላዊ ንድፍ ሐሳብ የትክክልና ስህተት እሳቤዎች የሚጠኑበት ነው። Haidt (2012) እንዳብራሩት፣ የሰዎች ሞራላዊ ፍርድ በተፈጥሮ የተገኙ ነገርግን በባህላዊ አውዶች የተቀረጹና ውስን ቁጥር ባላቸው ስነልቡናዊ መሰረቶች ይገነባል። በዚህም መሰረት Haidt (2012) የስነምግባር መሰረቶችን፡- እንክብካቤና ጉዳት (Care/harm), ፍትሐዊነት/አጭበርባሪነት (Fairness/Cheating)፣ ታማኝነት/ክህደት (Loyalty/Betrayal)፣ የስልጣን ግዛትና/አመጸኛ (Authority/Subversion)፣ ቅዱስና ርኩስ (Sanctity/Degradation)፣ ነጻነትና ጭቆና (Liberty/oppression) በማለት በስድስት ይከፍሏቸዋል። የጥሩ ስነምግባር መሰረቶች የግለሰቦችን ባህርይ ለመቅረጽ ምቹ መሆናቸውን Forrester (2002) እና Avichal (2023, 4) ገልጸዋል። በዚህ ትንተናም ከሞራላዊ ጥሰት የሚመልሱ ሥርዓቶች ተመርምረውበታል።

ሌላኛው ደግሞ መዋቅራዊ-ተግባራዊ ንድፍ ሐሳብ ነው። Brown (2013, 26) Durkheim ን ጠቅሰው በማኅበረሰብ ውስጥ የጋራ ትስስር የሚፈጥሩ የወል ስርዓቶች፤ የተሰሩት ዕርስ በርስ በተያያዙ የቡድኖች ሥነ ምግባራዊ ግንኙነቶች፣ በጋራ ባህርያትና ግንዛቤ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ይላሉ። ሃሳቡ ስለማኅበረሰብ የጋራ እሴትና ተግባቦታዊ ደንብ ይገልጻል። በተጨማሪም Wandi, Afnita, & Hefni (2021, 39-41)፣ Brown(2013,26) በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ያሉ ማኅበራዊ ስርዓቶች የቡድኑን የጋራ ስምምነትና ተጠቃሚነት እንደሚያሳይ ይገልጻሉ። በዚህ ትንተና ማኅበረ-ባህላዊ እሴትን የሚያስጠብቁ የማንጻት ሥርዓቶችን ተቋማዊ ፋያዳ ለመፈተሽ አገልግሏል። ሌላኛው የመንጻትና መርከስ ንድፍ ሐሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ Douglas (1966, 2002) ጥልቅ በሆኑ ማኅበራዊና ባህላዊ ስርዓቶች ላይ ይታያል፤ መርከስ ካለ ማኅበራዊ ‹‹ሥርዓት›› አለ ይላሉ። በዚህ ትንተና ከርኩሰት የሚያነጹ ስርዓቶችንና እሴቶች ይመረምራል።

### 3. መረጃ ትንተና፤ ርኩሰት የሚነጻባቸው እሴቶች

የባሶሊበን ማኅበረሰብ ርኩሰት ከሚሏቸው ተግባራትና ክስተቶች ለመጠበቅ፣ የንጽሕና እሴቶች አስፈላጊ ናቸው። Boudon (2017, 38) ማኅበራዊ እሴቶች ለማኅበራዊ አንድነት ምስረታ የሚረዱና የጥሩ/ንጽሕናና መጥፎ/ርኩሰት መገለጫ የሚታይባቸው መሆናቸውን ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር በዚህ ምዕራፍ ከርኩሰት የሚያነጹ ሥርዓቶች ተተንትነዋል።

### 3.1. ባህላዊ ማኅበራዊ የማንጻት እሴቶች

ተጠኚው ማኅበረሰብ ርኩሰት ብሎ ከሚያስባቸው ሁነቶች ለመጠበቅ ከሚጠቀሙባቸው እሴቶች መካከል ማኅበራዊ የማንጻት ሥርዓቶች ይጠቀሳሉ። ከዚህ በታች የቀረቡት መረጃዎች ለዚህ ማሳያ ናቸው።

#### 3.1.1. የመሐላና የኪዳን ቃላት

የመሐላና ኪዳን ቃላት ማኅበረሰቡ የርኩሰት ተግባር የፈጸሙትን ወደ ንጽሕና እንዲመለሱ የማድረጊያ መንገዶች ናቸው። ማኅበረሰቡ ሞራላዊ የርኩሰት ተግባራት ከሚላቸው መካከል የስርቆትና ግድያ ተግባራት እንደርኩሰት ይቆጠራሉ። በእነዚህ የሚከለከሉ ተግባራት የተጠረጠሩ ሰዎችን ጥፋተኛነት ለማረጋገጥ በቃለመኃላ ያረጋግጣሉ። ጥፋተኛው ‹‹እርም ይሁንብኝ›› ብሎ መኃላ በመፈጸም ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል። በሌላ መንገድ ደግሞ ጥፋተኛው ከተለዬ በኋላ ቂምና ጥላቻው እንዲወገድ በመሐላ እንዲታረቁ ይደረጋል። የገዳይና ሟች ቤተሰብ የልብ ቂምና ጥላቻ እንዳይኖር፤ ተጎጂው ወገን ለብቀላ እንዳይነሳሳ እርቅ በሚፈጽሙበት ጊዜ ቃላቸውን በመኃላ ያስራሉ። ‹‹እርቄን ባፈርስ የተጋደመው መሳሪያ ይውጋኝ፣ አንዱ ቢስተኝ ሌላኛው አይሳተኝ ብሎ ይምላል፤ እንደዚህ ብሎ ከማለ በኋላ ይህንን ቃሉን አፍርሶ መበቀል አይቻልም›› (ሚያዚያ 28፣ 2017 በቡድን ውይይት)። ይህ የስምምነት መፍጠሪያ መሃላ በመሆኑ ቃለመሐላቸውን ማፍረስ ርኩሰት ተደርጎ ይቆጠራል። Douglas (2002) ቃልኪዳን መጠበቅ ከፈጣሪ በረከትን ያስገኛል ይላሉ። በመሐላ እርቅ ካልፈጸሙ በጋራ ሥርዓቶች መሳተፍና መመገብ እንደስህተት ይታሰባል። በሌላ መንገድ በስርቆት የተጠረጠሩ፤ በሌሎች ሰዎች ድንበርና ሰብል ላይ ጉዳት ያደረሱ፣ በደል የፈጸሙ ሰዎች ከጥፋታቸው ነጻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ይጠቀሙበታል። ‹‹እኔ ይህንን ጥፋት አልፈጸምኩም፣ ይህንን ፈጽሜ ከሆነ ‹እንደዚህ ያጥፋኝ› በማለት የነደደውን እሳት በውሃ አጥፍቶ ቃሉን ይፈጽማል›› (ተ1[3]፣ መጋቢት 23፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። ይህ ራስን ከርኩሰት ተግባር ነጻ መሆንን የማረጋገጫ መንገድ ነው። የመሐላና የኪዳን ቃላት ሰዎችን ወደስምምነት የሚመልሱበት እሴት ነው።

#### 3.1.2. የእንስሳት ደም

የእንስሳት ደም (በዋናነት የበግ) ጤንነትን ከማስጠበቅ አንጻር የርኩሰት ኃይል ካላቸውና የእንስሳትንና ሰውን ጤንነት ከሚበክሉ የወረርሽኝ በሽታዎች ለመጠበቅ ሲባል፣ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ወይም ሰብልንና መልክዓምድርን ከሚያውኩና ከሚያምክኑ አደጋዎች (ለምሳሌ፡- ድርቅን፣ በረድን፣ ቸነፈርና ትል) ለመከላከል በሚል እምነት በደም ማፍሰስ የግስ ሥርዓት ተማጽኖ ለማካሄድና ርኩሰቱን ለማስወገድ የእንስሳት ደም ማፍሰስ ይተገበራል። ‹‹ግስ ሥርዓት›› ማኅበረሰቡ በመሰባሰብ አካባቢውን ሰብሉን ሰውን ከበሽታ ለመጠበቅ፣ አካባቢውን ከተፈጥሮ አደጋ ለማንጻት የሚከውነው ሥርዓት መጠሪያ ነው። ይህም ቀዬውን ሰላም በማድረግ ማኅበራዊ አንድነትን ለማስጠበቅ፣ የልብ ንጽሕና እንዲኖር የተጣላ እንዲታረቅ በማድረግ ረገድ ሰዎች በደም መፍሰስ ሥርዓቱ ማኅበራዊ ተግባቦት እንዲኖራቸውና ደሙ ፈውስ የሚያገኘው የመንፈስ ንጽሕናም ሲጠበቅ ነው ተብሎ ይታመናል። ከዚህ የተነሳ ደም ማኅበራዊ አብሮነትን ከሚያናጉ ክስተቶች ለማስጠበቅ ይረዳል። ‹‹…ደም በፍራጁ (በግሱ ሥርዓት ማለታቸው ነው) ሲፈስ አካባቢው ይጠበቃል፣ ሃገሩ ሰላም ይሆናል፤ ደሙ ከፈሰሰ በኋላ የባረከው ሰው በዕቃ የያዘውን ደም እንስሳቱን ይረጨዋል፤ በዚህ ጊዜ ሰውም ሆነ እንስሳቱ ከበሽታ ይፈወሳሉ›› (ተ1፣ ጥቅምት 15፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። ከዚህ አንጻር ማኅበረሰቡ የአብሮነት ስነልቡናዊ ተስፋውን ለማቆየት የሚመኝበት በመሆኑና የተከሰተ ማኅበራዊ ያለመግባባት ችግር ካለ ሞራላዊ ጥሰቶች እንዲስተካከሉና በማኅበራዊ እሴቶች እንዲመለሱ በማድረግ በሥርዓቱ ተቀላቅለው ይሳተፋሉ። Georgoudi,(2017, 112) በግሪክ እምነት እባብ የሞተበት ቤት ሰዎችን ያረክሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ቤቱ በሱፍ፣ በጨው፣ በውሃ ከታጠበ በኋላ የአሳማ ግልገል ደም ለመስዋት ሥርዓት ይተገበራል ይላሉ፤ ይህ ሃሳብ የመስዋዕት ደም በመስዋዕት የሚፈጸም የማንጻት ሥርዓት መሆኑን ያሳያል።

በሌላ መንገድ የእንስሳት ደም (በብዛት የበግ) የሰዎችን ቂምና ጥላቻ የማስወገድ ሰላም የማስፈን ሞራላዊ እሴትን የሚያስጠብቅ ነው ተብሎ ስለሚታመን በእርቅ የቃለመኃላ ማስፈጸሚያ ሥርዓት ላይ ደም መመላለስ እንዳይኖር ብቀላን ለማንጻት በእርቁ ላይ የበግ ደም እንዲፈስ ይደረጋል። ይህም ሞራላዊ መመሪያን ከማስጠበቅ አንጻር የማኅበረሰብን እሴትና ደንብ የሚጥሱ ተግባራትን ለማንጻት የሚረዳውን የጋራ መግባቢያ ደንብ ያሳያል (Douglas 2002, 134)። በዚህ ጊዜ የሚፈሰው ደም ፍቅርን የሚመልስ በሰዎች መካከል የነበረው ቂም እንዲወገድ ከታረደው የበግ ስጋ አብሮ የመመገብ ሥርዓት ይተገበራል። የበጉ ደም በሰዎች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ከመመለስ ባለፈ የፈሰሰውን የሰው ደም መበቀያና የማንጻት ምሳሌ ነው።

---

[3] ተሳታፊ አንድ ማለት ነው ፡

### 3.1.3. ምርቃን

ምርቃን ተስፋና ፀሎት ነው ተብሎ ስለሚታመን ከአስከፊ ተግባራት ለመንጻት፤ በታላላቅ አባቶችና የኃይማኖት አባቶች በመመረቅ ተስፋቸውን ያለመልማሉ። ሰዎች ድምጻቸውን ሳያሰሙ ልባቸውን ለመራቂው በመስጠት መዳፋቸውን በመዘርጋት መራቂው ሲመርቅ ‹‹አሜን›› በማለት ይቀበላሉ።
Douglas (2002) ‹‹የእስራኤል ሰዎች የእንስሳቶቻቸውን እና መልክዓምድራቸውን ጤናማነት ለመጠበቅ በከበራዊ የማንጻት ሥርዓቶች ሳይሆን በጸሎት በታጀበ ምርቃንና ተማጽኖ ከፈጣሪ በመገናኘት ነው›› ይላሉ። የዚህ ጥናት አካል የሆነው ማኅበረሰብም በውቂያ ወቅት በረከትን ከሚያሳጡ ርኩስ መናፍስት ለመጠበቅ፣ የሰዎችን ጤናማነት ለመመኘት የተለያዬ መጥፎ የሕይወት አደጋ(ርግማን) የማንሳት ኃይል እንዳለው ይታመናል። ‹‹ምርቃን ጤፉ ከመወቃቱ በፊትም ሆነ በኋላ እንተገብረዋለን፤ መራቂው በእድሜ ከሌላው የሚበልጥ ወይም የኃይማኖት አባት ካለ ደግሞ ቄስ ይመርቃል፤…ምርቱ የተትረፈረፈ እንዲሆን፤ ስራውን በሰላም አስጀምሮ በሰላም እንዲያስጨርሰን፤ የጤና ቀለብ እንዲሆን ፈጣሪን በጸሎት እንጠይቃለን›› (ተ2፣ ህዳር 28፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። የምልጃ ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ የምግብ ማዕድ መኖር አለበት። ‹‹ብሩክ ሁኑ፣ እድሜውን ጤናውን ይስጣችሁ፤ አምላክ ሥራውን በሠላም አስጀምሮ በሰላም ያስጨርሰን፤ በመካከላችን ያመካክረን እንጅ አያፈካክረን እህሉን ነስቶ አይጣላን›› (ታህሳስ 25፣ 2017 በመስክ ምልከታ) በማለት መራቂዎች አምላካቸውን ሲማጸኑ ሌሎች ‹አሜን› እያሉ ይቀበላሉ። በዚህ ጸሎት ምርቃን ፍቅርና ሰላምን፣ በረከትን በመመኘት ፈጣሪያቸውን ይማጸናሉ።

በተጨማሪም በደም ማፍሰስ ሥርዓቶች ሂደትም ‹‹የሰላም፣ የፍቅር ደም ያድርገው፤ ጤናውን ሃብቱን ይስጠን፣ አካባቢውን ይጠብቅልን…›› (ተ3፣ መጋቢት 29፣ 2017 በቃለመጠይቅ) በማለት ከፈጣሪያቸው በልመናና ጸሎት የታጀበ ምርቃትን ይፈጽማሉ። ይህም ጤንነትን የሚጎዳ በሽታ እንዲወገድ የሚፈጸም ተማጽኖና ልመና ነው።

### 3.1.4. ስለታማ የብረት ቁሶች

ስለታማ ነገሮች ማህበረሰብ እደርኩሰት ከሚያስባቸው መናፍስት የማስጠበቅ ሚና እንዳላቸው ይታሰባል። በረከትን የሚነሳን የርኩሰት ኃይል ለማስወገድ በውቂያ ወቅት ምርቱ በርኩስ መንፈስ እንዳይቀንስ በሚል እምነት ጠባቂ ቁሶች ምርት ከተሰበሰበ በኋላ በተሰበሰበው ምርት መሀል የተለያዩ ስለታማ ነገሮችን ይጠቀማሉ። ‹‹ወንዶች ከላይ ወደታች እና ከግራ ወደቀኝ የተቆለለውን ምርት ክብ በማስመር፣ ምሳርና ሌሎች ስለታማ ነገሮች ከመሃል እንዲገቡ ይደረጋል›› (ተ4፣ ታህሳስ 20፣ 2017 በቡድን ውይይት)። በዚህ አውድ ስለታማ ነገሮችን ርኩስ መንፈስ አይቀርባቸውም የሚል እምነት ስላለ የምርቱን በረከት ያስጠብቃል። በተጨማሪም ‹‹የበረድ አደጋ በተከሰተ ጊዜ በእሳት የጋለ የማረሻ ብረት፣ ስለታማ የሆኑ እንደመጥረቢያ ማረሻ ነገሮችን በረድ መጣል ሲጀምር በእሳት በማጋል ወደ ውጭ በመወርወር በረዱ እንዲነሳ ይደረጋል›› ተ5፣ ሐምሌ 10፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። በሌላ መንገድ አራስ ሴቶች ከወለዱ በኋላ ስለታማ ነገሮች ከአጠገባቸው ያስቀምጣሉ። ከዚህ አንጻር ስለታማ ቁሶች ርኩስ መንፈስን የመከላከል ኃይል አላቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ጤንነትን ኪያሳጣና ተፈጥሯዊ አደጋ ይጠብቃሉ ተብሎ ይታመናል።

### 3.1.5. የሆሮጋዙ/አምቦ ጠበል

የባሶሊበን ማኅበረሰብ ደህንነታቸውን ጤናማ ለማድረግ ከሚተገብሯቸው ሥርዓቶች መካከል የሆሮጋዙ እምነት ጠበል ይጠቀሳል። Blidstein (2017) እና Duschinsky (2016) ርኩሰት ከበሽታ፣ የማጥቃት ሃይል ካላቸው ርኩስ መንፈሶችና አካላዊ ርኩሰቶች ጋር የሚገናኝና ከእነዚህ ሁነቶች በመንጻት ሥርዓትን ለመመለስ የአምልኮ ስርዓቶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያስረዳሉ። ‹‹የሆሮጋዙ ጠበል›› የሚለው ቃል የእምነቱ መጠሪያ ነው። ይሁን እንጂ ‹‹አምቦ ጠበል›› በማለት በተጨማሪነት ማኅበረሰቡ የሚጠቀምበት ሲሆን ስያሜው ጠበሉን ለመጠቆም ነው። አምቦ ጠበል/ሆሮጋዙ/ ከፈዋሽነቱ ፋይዳ የተነሳ ጠበል በሚል ይጠሩታል። ጠበሉ በደን ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ሰዎች በጠበሉ ለመጠቀም በቦታው የሚሄዱት በብዛት በሰኔ መግቢያ ወር፣ በጥቅምት ወር እና በጳጉሜ ወር የተፈቀደ ነው።

በዚህ እምነት በመጠቀም የመፈወስ ልማዱ ከክርስትና እምነቱ ጠበል የተለዬ፣ ጽላት የሌለውና በሃይማኖታዊ አባቶች ተባርኮ ኃይማኖታዊ እውቅና የሌለው መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ። የሆሮጋዙ/አምቦ ጠበል ከኃይማኖታዊ ጠበል የተለዬ ስለመሆኑም የተለያዩ ማሳያዎች አሉ። መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልጹት፡- ‹‹ሰው ወደ ጠበሉ ሲሄድ የተሳሉት ነገር ካለ እሱን ይወስዳሉ፤ በቦታውም ከተወሰደው መቅመሳችን ስለማይቀር የምናርድ ከሆነ ሰኔ ጾም ሳይገባ እንሄዳለን፤...ሌላ ምግብም ቢሆን የተገኘውን በልተን ጠበሉን መጠጣት እንችላለን፤ (ተ1፣ ተ6፣ ተ7 እና ሌሎች ቡድን ሰኔ 20፣ 2017 ከተካሄደ ውይይት)። ሃሳቡ እንደሚያሳየው የሰዎች ትኩረት ከጠበሉ የማንጻት ፋይዳ እንጂ ምግብ ከመመገብ በኃላም መጠጣት እንደሚቻል ይገልጻሉ።

የአምቦ ጠበሉ ከሃይማኖታዊ ሥርዓት በተለዬ ተበልቶ መጠጣቱ ቤተክርስቲያናዊ አለመሆኑን ‹‹ጎጃም ሲታመም፤ ምግብ ተበልቶ ይጠጣል ጠበል›› (ተ7፣ መጋቢት 20፣ 2017 በቃለመጠይቅ) በማለት ገልጸዋል። በመሆኑም የሆሮጋዙ ጠበል ከሃይማኖታዊ ጠበል ህግ የተለዬ መሆኑን የሚገልጽ ሃሳብ ነው።
ተጠኚው ማኅበረሰብ ይህንን ጠበል በመጠቀም የእንስሳትን የመንቀዥቀዥ ባህርይ ለማስተካከል፣ መውለድ የማይችሉ ሰዎችንና እንስሳትን እንዲወልዱ ለማስቻል፤ የሆድ ውስጥ ደዌን ለማንጻት ይረዳል የሚል እምነት አለ። ይህንን ፋይዳ ለማግኘትም ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ጠበሉን በመርጨትና በመረጨት፣ የስለት (የሚበሉና የሚጠጡ ምግቦችን፤ ለመስዋዕት የሚቀርቡ እንስሳትን) መባ በማቅረብ ይታመንበታል።

### 3.1.6. አባይ ጠበል

አባይ ወንዙና ጠበሉ የሚገኝበትን ቦታ የሚያመላክት ሲሆን ጠበል የሚባለው ደግሞ ከወንዙ የሚቀዳውን ፈዋሽ ውሃ ነው። የአባይ ጠበል ማኅበረሰቡ የማንነት ወሰኑን የሚረዳበት ድንበሩ ከመሆኑ ባሻገር ፈውስን ለማግኘት፣ ምኞትን ለማሳካት፣ ዓለማዊ ሕይወታቸውን የተስተካከለ ለማድረግ በጠበልነት ይጠቀሙበታል። በመሆኑም ተጠኚው ማኅበረሰብ በውሃው ከሚያገኘው የፈውስና በረከትን የማስጠበቅ ሚና አንጻር ‹‹የአባይ ጠበል›› በሚል ስያሜ በመጠቀም ጠበሉን ከአላስፈላጊ ክስተቶች ለመንጻት ይገለገልበታል። ማኅበረሰቡ ከአባይ ጠበል ጋር ያለውን ትስስር እንዲያጠናክርለትና ልመናው እንዲሰማለት የሚፈልገው እንዲሳካለት በቦታው ስለት መሳልና በስለት መጠየቅ፣ ጥምቀት መፈጸም ጠበሉን ከወንዙ ቀድተው በማምጣት ቤታቸውንና ሰብላቸውን ሁሉ መርጨት ርኩሰትን ይከላከላል የሚል እምነት አላቸው።
በዚህ መንገድ እንደሆሮጋዙ ጠበል ሁሉ የአባይ ጠበልም የሰዎችን ጤና ከክፉ አደጋ ሁሉ የማስወገድ ሚና እንዳለው ስለሚታመን በመኖሪያ ቤት መውጫና መግቢያ በር ላይ መስቀል፣ ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳትን ወስደው ለወንዙ ማቅረብ የተለመደ ተግባር ነው። የአባይ ጠበል ፈውስን፣ በረከትንና ለመውለድ ከሚከለክል ችግር፣ ሰዎች ከማይፈልጓቸው መጥፎ ድርጊቶች ለመንጻት እንደሚረዳቸው ይታመናል።
በመሆኑም ተጠቃሚው ሰው ምኞቱ እንዲሳካ ጸሎቱ እንዲሰማ የተለያዬ ስለት ይወስዳል ‹‹…መኪና ብገዛ ወረቴ ቢጨምር፣ ምርቴ ቢበረክት፣ መውለድ ብችል ይሄን አቀርባለሁ ብሎ የተሳለውን ይወስዳል፤ ዶሮ ወስዶ እስከነፍሷ ወደ ባህሩ መወርወር፣ ገንዘብ ወስዶ ተቀባይ በሌለበት ከወንዙ መሃል መጣል በሬ ከሆነም ወስዶ አርዶ በማካፈል ሙብላትና ትርፉን ወደ ወንዙ አጠገብ በመጣል ስለቱን ያቀርባል። ዶሮ፣ በሬ፣ ፍየል፣ አረቂ፣ በግ፣ ወተት፣ እንጀራ በድቁስ…ለስለት ይወሰዳል›› (ተ5፣ ጥቅምት 5፣ 2018 በቃለመጠይቅ ወቅት)። ስለሆነም ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳትን፣ ገንዘብ፣ ምግብና መጠጥ በማቀርብ ልመናቸው እንዲሰማ ልቡናው እንዲጽናና ተስፋው እንዲለመልም መማጸኛ በማድረግ ይጠቀሙበታል።

## 3.2. ኃይማኖታዊ የማንጫ ሥርዓቶች

ከርኩሰት ለመንጻት ከሚረዱ እሴቶች መካከል ኃይማኖታዊ ስርዓቶች ይጠቀሳሉ። Durkheim (1995) እና Douglas (2002) ኃይማኖታዊ የማንጻት ሥርዓቶችና ሕጎች ማኅበራዊ ሥርዓትን ለመጠበቅ፣ ቡድናዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ ሞራዊ መመሪያዎችን ለመጠበቅ፣ ፈውስን ለማግኘትና ማኅበረሰቦች ቅዱሱን ከርኩሱ በመለየት እንዲሞሩ የሚረዱ መሆናቸውን ይገልጻሉ። ተጠኚዎቹ ሥነምግባርንና ጤናን ከሚያበላሹ ተግባራት ለማንጻት ደግሞ የተለያዩ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ይጠቀማሉ።

### 3.2.1. ንሰሐ

በማኅበረሰቡ ዘንድ በሰዎች ላይ ቁሳዊ ጉዳት ማድረስ፣ ግድያ መፈጸም፣ በቂም ተነሳስቶ ሰዎችን በጥላቻ መመልከት፣ ስርቆት መፈጸም፣ ክህደትና የሃሰት መኃላ መፈጸም የርኩሰት ተግባራት መሆናቸው ይታመናል። Douglas (2002) በሚያነጹ ተግባራት ከሥነምግባራዊ ስህተቶች መመለስ እንደሚቻል ይጠቅሳሉ። በኃይማኖታዊ ህግ ውስጥ እነዚህ ሞራላዊ የርኩሰት መገለጫዎች ከኃጢያት ርኩሰት ጋር የሚገናኙ ናቸው። ከዚህ አንጻር የኃጢያት ርኩሰትን ለማንጻት ደግሞ ንሰሐ በስጋዊ ፍላጎት የተሰራን መጥፎ ሥራ ለነፍስ በደል እንዳይሆን በንሰሐ መታጠብ እንደሚያስፈልግ ይታመናል። የዚህ የመታጠብ እሳቤ የተሰራ ኃጢያትን ከማስወገድ፣ ወደ ጥፋት ካለመመለስ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ በልቡናዊ ኃጢያት የሚተገበሩትንና ልቡናን ከሚያቆሽሹ ሁነቶች መንጻትንም ያካትታል። በመሆኑም ሰው መግደልና ሌሎች ጎሊናዊ ሰብዕናን የሚያቆሽሹ ተግባራት ሲፈጸሙ በንሰሐ መንጻት እንደሚገባ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ። ይህንን ሃሳብ ‹‹ኃጢያት በንሰሐ ቆሻሻን በውሃ›› (ተ1፣ ጥቅምት 6፣ 2018 በቃለመጠይቅ ወቅት) በሚል አባባል ይገልጹታል። Durkheim (1995, 312**)** የመንጻት ሥርዓቶች የሚፈጸሙት ቆሻሻን በቀላሉ ለማስወገድ ሳይሆን ሞራላዊ አንድነትን ለመፍጥርና የደንብ ጥሰትን በማስተካከል ማኅበራዊ አንድነትን ለማጠናከር መሆኑን ይገልጻሉ። ይህ

ሃሳብ የሚያሳየው የኃጢያት ተግባር አካላዊ ሳይሆን ከሞራልና ከስነልቡና ጋር የተያያዘ በመሆኑ በትጥበት ሳይሆን በንሰሐ የሚነጻ መሆኑን ነው፡፡

‹‹አንድ ሰው ደም ከተቃባ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲገባ አይፈቀድም፤ ንስሐ ይሰጠውና ንስሐው እስከሚያበቃ ድረስ ከቤተክርስቲያን ግቢ ውጭ ሆኖ የንስሐ ጊዜውን ሲጨርስ ንስሐ ቄደር ይደገምለታል›› (ተ8፣ የካቲት 29፣ 2017 የተደረገ ቃለ መጠይቅ) በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ንሰሐ ከግድያ ኃጢያት እንደሚያነጻ ያስረዳሉ፡፡ Koenig (2012) ንስሐ ግለሰቡ ከፈጣሪው ጋር ያለውን ግንኙነት በማደስ በውስጡ የሰላምና የተስፋ ስሜት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ኃጢያትን ለኃይማኖት አባት በመናዘዝ በንጹሕ ልቡና ይቅርታ ማድረግንና መመለስን ከርኩሰት እንደመንጻት ይታሰባል፡፡

### 3.2.2. ጸሎትና ምህላ

ርኩሰት ከፈጣሪ ወይም ከመናፍስት ጋር ያለውን ግንኙነት ያሻክራል ተብሎ ስለሚታመን በጸሎትና በልመና መማጸን የተለመደ ነው፡፡ ጸሎት ግለሰባዊና ማኅበራዊ ሲሆን፣ ምህላ ደግሞ ቡድናዊና ሰዎች ከማይፈልጉት የጋራ ችግር ለመንጻት የሚያቀርቡት ቡድናዊ ተማጽኖ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች ከአስቸጋሪ ወቅታዊ ፈተናም ሆነ የልቡና ርኩሰት ለመመለስ ይፈጽሙታል፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ተፈጥሯዊ የሆኑ አደጋዎች፣ በሽታ፣ በተከሰተ ጊዜ የታላላቅ አባቶች ጸሎትና ምህላ ወይም የምልጃ ጸሎት ፈዋሽ በመሆኑ በመሰባሰብ ይፈጽማሉ፡፡ የምልጃ ጸሎቱ ርኩሱን የመቀደስ፣ ያጣውን የማስገኘት፣ የታመመውን የመፈወስ፣ የረከሰውን የማንጻት ኃይል ስላለው በቡድን ጸሎትና ምህላ በመጠየቅ መንጻት እንደሚቻል በማመን ይተገበራል፡፡ Douglas (2002) ‹‹በእስራኤል ባህል ለጸሎት ትልቅ እምነት እንዳላቸውና ወታደሮች በካምፓቸው ውስጥ የቡድናዊ ጸሎት ያደርሳሉ›› ይላሉ፡፡ ማህበራዊ ጸሎትና ምህላ ሲፈጸም እያንዳንዱ ሰው ከክፋትና ተንኮል ህሊናውን በማንጻት፣ ፍቅርን በማሰብ፣ ስለክፉ ነገር መወገድ በመጸለይ፣ በኃዘንና በስግደት፣ በተመስጦ በመጸለይ አላስፈላጊ ነገሮችን መከላከል እንደሚቻል መረጃ አቀባዮቼ ገልጸውልኛል፡፡ ‹‹በአንድ ወቅት ጊዜውን አላስታውስም አንከሊስ የሚባል በሽታ ተከሰተና በየአካባቢው ያሉ የኃይማኖት አባቶች መስቀል ይዘው፣ ሰዎች ተሰባስበው የምህላ ጸሎት በማድረጋስና አባቶች ማዕጠንት አጥነው በሽታውን ማስወገድ ተችሏል፤ ኮቪድ በተከሰተ ጊዜም ሰው ሁሉ በቡድን በመሰባሰብ ወደ ፈጣሪ በጸሎት በመጠየቅ አስቸጋሪው ወቅት ታልፏል›› (ተ6 መስከረም 28፣ 2018 በቃለመጠይቅ)፡፡ ይህን ሃሳብ Bandak (2017) ‹‹ጸሎት መከራን ለማስታገስ፣ ለፈውስ ወይም የተሻለ ሕይወት ተብሎ ወደሚታሰበው ነገር ለመምራት ተስፋ የሚደረግበት ሲሆን፤ ሰዎች ስለእምነታቸው ብቻ ሳይሆን ከሚያስጨንቃቸው ነገር ለማስወገድ ካላቸው ፍላጎት፣ የሚያቀርቡት ተማጽኖ ነው›› ይሉታል፡፡ ከዚህ የተነሳ ቡድናዊ የጸሎት ሥርዓቶች አስከፊ ማኅበራዊ ችግሮችን ለማስወገድ የሚታመኑና የሚፈጸሙ ናቸው፡፡

### 3.2.3. ጠበል/holy water

ጠበል ከህመም ለመፈወስ፣ በረከትን ለማስጠበቅና ርኩስ መንፈስ ኃይላትን ለማስወገድ እንደሚረዳ ስለሚታመን ዋና የማንጫ መንገድ ተደርጎ ይታመናል፡፡ Douglas (2002, 95) ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ውጫዊና ውስጣዊ የርኩሰት ኃይላትን የሚያነጹ የማኅበራዊ ዘዴዎች አካል ናቸው ይላሉ፡፡ በመሆኑም ኃይማኖታዊ ጠበል በኃይማኖት አባቶች ጸሎት የተደረሰበት በመሆኑ፣ በረከትን ከሚነሳ ርኩስ መንፈስ፣ የሰዎችን ጤና ከሚጎዳ ረቂቅ የክፉ ዓይን ጨረር ያነጻል ተብሎ ይታመናል፡፡ Baheretibeb, et.al (2025) ‹‹በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቀሳውስት ጠበልን በመጠቀም በኃይማኖት ላይ የተመሰረተ የተለያዩ መንፈሳዊ የማንጻት ሥርዓቶች ይፈጽማሉ›› ይላሉ፡፡ በመሆኑም ጠበል በመጠመቅ፣ በመጠጣትና በመረጨት ተግባራዊ በማድረግ ርኩስ መናፍስትን ያስወግዳል፣ ተብሎ ይታሰባል፡፡

በረከትን ለማስጠበቅ ደግሞ በሰብል ውቂያ ጊዜ ከክምሩ ላይ የኃማኖታዊ ጠበል ይጨመራል፤ ይህም ምርቱ ከርኩስ መንፈስ እንዲጠበቅ ነው፡፡ በአውድማ ላይ በሚረጨበት ወቅት ከግራ ወደ ቀኝ የአውድማውን ክትር ዙሪያውን አንድ ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ በመዞር ነው፡፡ ከግራ ወደቀኝ የሚረጨበት ምክንያት መልካምነትን፣ ተስፋን የመግለጥ ሚናን ለማሳየት እና የንጹሕ ተግባር መገለጫነቱን ማሳያ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ የሚዞሩት ደግሞ አውድማ በቤተክርስቲያን ስለሚመሰልና የስላሴን አንድነትና ሦስትነት ለማመልከት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ የመኖሪያ ቤትን ለማደስ አዲስ ቤት በሚሰራበት ወቅት ቀድሞ የሚሰራበት ቦታ የሚባረከው ጠበል በመርጨት ነው፡፡ ይህም ለሰዎች ጤንነት ስጋት ከሚፈጥር ርኩስ መንፈስ ይጠብቃል የሚል እምነት በመኖሩ ነው፡፡ በተጨማሪም የበቀለ ሰብል ትል ሲበላውና ሲደርቅ ጠበል በመርጨት የማስወገድ ተግባር ይፈጸማል፡፡ የወለዱ አራስ ሴቶች ሴት ሲወልዱ በአስራምስተኛውና ወንድ ሲወልድ በሰባተኛው ቀን ካህኑ ውሃው ላይ ጸሎት ካደረሱበት በኋላ ያጠምቃሉ፡፡ ይኼም አራሷን ርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባት ጤናዋን ለመጠበቅ ሲሆን በሌላ መንገድ ደግሞ የአራስነት ንክኪን ለመፍቀድ ነው፡፡ Douglas (2002) እንደሚሉት በቤምባ ያሉ ሴቶች በማንኛውም ንክኪ በማይፈቅድ ፈሳሽ ወቅት ላይ ከሆኑ የሚሰሩት ምግብ ህመም ያመጣል የሚል እምነት ስላለ መንጻት የግድ ነው ይላሉ፡፡

### 3.2.4. በጥምቀት

በኃይማኖታዊ ጥምቀት ለመንጻት ሊነጻ እንደተፈለገው ጉዳይ በተለያዩ መንገድ ይፈጸማል። አራስ ሴት ከሌሎች ሰዎች፣ ቁሶች ጋር በሚኖራት ንክኪ ምክንያት በሌሎች ሰዎችና ቁሶች ርኩሰት እንዳታስከትል በሚል እምነት፤ በጤናዋ ላይም ርኩስ መንፈስ እንዳይደርስ ጥምቀት ይፈጸማል። ‹‹በአሁኑ ጊዜ በሃዲስ ኪዳን የቤተክርስቲያን ቅዱስ መጽሐፍ ስርዓት የሚያስገድድ ባይሆንም ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ አንዲት ሴት ወንድ ከወለደች በሰባተኛው ቀን ሴት ከወለደች ደግሞ በአስራ አምስተኛው ቀን በውሃው ላይ የፀሎት ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ እንድትጠመቅ ትደረጋለች›› (ተ8፣ ጥር 10፣ 2017 ዓ.ም በቃለመጠይቅ)። ይህም እርኩስ መንፈስ በወላዷ ላይ ከፀናባት አስቸጋሪ ስነልቦናዊ ቀውስ እና ሌሎች የጤና ችግሮች ይፈጠራሉ በሚል እሳቤ ነው። ጥምቀቱ ከእርኩስ መንፈስ/አጋንንት ያርቃል በሚል እምነት እንደሚተገበር ያስረዳል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በባህሉ ውስጥ የማንጻት ስርዓቱ የቀጠለና በጠበል ጥምቀትና በጸሎት የሚከወን ሲሆን፣ አዋላጅ የሆነች ወይም እትብት የቆረጠች ሴት ከአራሷ ጋር በጠበል የመረጨት ሥርዓት እንደሚፈጸምላት ይገልጻሉ።

መንታ ወንድና ሴት ህጻናትን የወለደች ሴት ከሆነች ንጽሕና ስርዓት የሚፈጸመው የሴቷ ደንብ በሚፈቅደው መንገድ ነው። ‹‹ህጻኗ የልጅነት ጥምቀት የምታገኝበትን ጊዜ በመጠበቅ ወላዷ ጠበል ትረጫለች›› (ተ8፣ መጋቢት 23፣ በቃለመጠይቅ)። ከዚህ የመንጻት ሥርዓት ጊዜ በኋላ እንዳትተገብራቸው ከሚከለከሉ ነገሮች ሁሉ መሳተፍ ይፈቀድላታል። ‹‹ከአራስ ቤት በጠበል መረጨት ወይም መጠመቅ ሳይተገበር የሰንበት ዱቄት ወስዶ ማቀላቀል አይቻልም›› (ተ3፣ ህዳር 3፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። ‹‹የሰንበት ዱቄት›› ቅዳሜና እሁድ በቤተክርስቲያን ለምዕመናን ዝክር ለሚሆን መክለፍት(ዳቦ) ከሰዎች የሚሰበሰብ ዱቄት ነው። ይህን ለመተግበር አራሷ በጠበል መንጻት አለባት ተብሎ ስለሚታመን ነው። ይህ ጊዜዊ መንጻት ቢሆንም ሙሉበሙሉ የምትነጻው ክርስትና ካስነሳች በኋላ ነው። በዚህ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት ይፈቀዳል። ይህ የመንጻት እሳቤ በአሁኑ ወቅት ሲተገበር የኃይማኖት አባቶች የኦሪታዊ ሥርዓት ነው ቢሉትም በማኅበረሰቡ ዘንድ ግን ይተገበራል።

## 4. ማጠቃለያ፣ ውስንነትና የጥናቱ አበርክቶ ማብራሪያ

### 4.1. ማጠቃለያ (Conclusion)

በዚህ ጥናት የባሶሊበን ማኅበረሰብ ማኅበረ-ባህላዊ እሴቱን ለማስጠበቅ የሚጠቀምባቸው የማንጻት ልማዳዊ ሥርዓቶች ተመርምረዋል። በትንተናው እንደተገለጸው ማኅበረሰቡ እንደርኩሰት የሚያስባቸውን ሁነቶች ለማንጻት ባህላዊ ማኅበራዊና ኃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በመጠቀም መሆኑ ተብራርቷል። ማኅበራዊ የማንጻት ሥርዓቶች በባህሉ የተቀረጹ ሲሆኑ፤ የመኃላና የኪዳን ቃላት፣ ስለታማ ቁሶች፣ ምርቃት፣ የእንስሳት ደም፣ ልማዳዊ ጠበሎችን (የሆሮጋዙና አባይ ጠበል) በመጠመቅና በመረጨት አካላዊና ስነልቡናዊ ጤናቸውን ለመጠበቅ እንደሚረዱ ተተንትኗል። በኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ደግሞ የጠበል፣ የጥምቀት፣ የንሰሐ፣ የምህላና ጸሎት ሥርዓቶችን በመጠቀም የማንጻት ሥርዓቶች እንደሚፈጸሙ ጥናቱ ያሳያል። ከእነዚህ የማንጻት ሥርዓቶች አንጻርም ይህ ጥናት ሁለት ዋና ዋና ግኝቶችን ይፋ አድርጓል። የመጀመሪያው የማንጻት ሥርዓቶች ጤንነትን ለማስጠበቅ የሚፈጸሙ መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን፣ በልማዳዊ ጠበል እና በኃይማኖታዊ ጠበል መጠመቅና መረጨት፣ የእንስሳት ደም በማፍሰስ በሽታን ማስወገድን ይፈጽማሉ። ሁለተኛው የሚያነጹ ሥርዓቶች ሞራላዊ እሴቶችን በመገንባት የዕርስ በዕርስ ትስስርን ለማጠናከር ይረዳሉ። በዚህም ንሰሐ፣ ጸሎት ሥርዓቶች፤ በእንስሳት ደም በማፍሰስ እርቅ መፈጸም፣ የቃለመኃላ ሥርዓቶች ማሳያዎች ናቸው። ይህ ሃሳብ Bogaert (2025) የሚያረክሱ ሁነቶች ማኅበረሰብ ለእሴቱ ቁጥጥር (Social control) እንዲያደርግና በሚያነጹ ሥርዓቶች እሴቶች እንዲገነቡ ይረዳል ከሚሉት ሃሳብ ጋር ይስማማል። በጥቅሉ የሚያነጹ ሥርዓቶች:- ማኅበራዊ ውህደትን ለመፍጠር፤ አንድነትን ለመገንባት፣ የእርስበእርስ ትስስርን ለማጥበቅ የሚረዱና ርኩሰት ተብለው ከሚታሰቡ ሞራላዊ ጥሰቶች ለማስተካከል፣ በሽታን ለማስወገድ፣ በረከትን ለማስጠበቅ፣ ከአላስፈላጊ ሁነቶች ለመጠበቅ የሚረዱ በመሆናቸው የማንነት መገለጫ እሴቶች እንዲገነቡ የሚረዱ መሆናቸውን (Cossu, 2024 & Gray et al, 2022) ጥናቱ ያሳያል።

### 4.2. የጥናቱ ውስንነት (Limitation)

የዚህ ጥናት ውስንነት:- ከበታ እንጻር በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚገኙ ሌሎች ወረዳዎችን አለማካተቱ ነው። ይህም የተጠኚዎች የማንጻት ሥርዓቶች ሌሎች አካባቢዎችን ሙሉ ለሙሉ ሊወክሉ አለመቻላቸው ነው። ሌላኛው ደግሞ የሚያነጹ ልማዳዊ ሥርዓቶች በትውልድ መካከል ካላቸው ቅብብሎሽ አንጻር ለውጦች ይስተዋላሉ። ነገርግን ይህ ጥናት ለውጥና ቀጣይነትን አለመመርመሩ ሌላኛው ውስንነት ነው።

### 4.3. የጥናቱ አበርክቶ ማብራሪያ (Implication)

ይህ ጥናት ሁለት ዋና ዋና አበርክቶዎች አሉት። የመጀመሪያው በጥናቱ ከተገለጹት ንድፍ ሃሳቦች አንጻር በ Douglas (2002) የመንጻትና መርከስ ቲዎሪ ማኅበረሰብ ርኩሰት የሚላቸውን ተግባራት ለማንጻት፣ በማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ እሴትን ለማስጠበቅና ለመመለስ ከበራዊ ሥርዓቶች አስፈላጊ መሆናቸውን ጥናቱ የመረመረ በመሆኑ አዲስ እይታ አበርክቷል። ከሞራላዊ መሠረቶች ንድፍ ሃሳብ አንጻር Barrow (2007) እና Timmons (2013) አንድ ማኅበረሰብ ትክክል እንደሆኑ የሚጠብቃቸውና የሚያከብራቸው መልካም እሴቶች እና በተቃራኒው ደግሞ ስህተት ስለመሆናቸው የተከለከሉ ተግባራት እንዳይፈጸሙ የሚያደርጉ እሳቤዎች የሚለይበት መሆኑን የጠቀሱትን ሃሳብ ማሳየቱ የማኅበረሰቡን መገለጫ ዕውቀት ያሳያል። ሌላኛው ደግሞ ማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓቶች ውስጥ ማኅበረሰብ የሚከለክላቸውና የሚፈቅዳቸውን ተግባራት ማስረዳት በመቻሉ ለልማት ፖሊሲ አውጪዎችና ለባህል ተመራማሪዎች መነሻ ሃሳብ አሳይቷል።

### 4.4. ምክረ ሀሳብ (Recommendation)

ማኅበረ-ባህላዊ እሴቶችን ከሚያረክሱ ሁነቶች የሚያነጹ ሥርዓቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጡ የመጡበት ሁኔታ እንዳለ ከመረጃ አሰባሰብ ሂደት ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም ሌሎች ተመራማሪዎች ለውጥና ቀጣይነትን በሚመለከት፤ በመመርመር መሰነድ ቢቻል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሞላ ጀንበሬ። (2009) ። *የነውር እሳቤ በሊቦከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት* [ያልታተመ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ]፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

በልስቲ ውቤ። (2011) ። *ደም አድርቅ የግጭት አፈታት ስርዓት በባሶ ሊበን ወረዳ* [ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ያልታተመ]፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

አያል ዋሴ። (2011 ዓ.ም) ። *ነውር እንደ ልማዳዊ ህግ በደራ ወረዳ ማህበረሰብ* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ]፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

የባሶ ሊበን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት። (2009) ። *ባህልና ኪን* [ያልታተመ]።

Antohin, A. E. (2014). *Expressions of sacred promise: Ritual and devotion in Ethiopian Orthodox praxis* (Doctoral dissertation, UCL (University College London)). UCL Discovery. https://discovery.ucl.ac.uk/

Aspen, H. (2001). *Amhara traditions of knowledge: Spirit mediums and their clients* (Vol. 58). Otto Harrassowitz Verlag.

Avichal. (2023). *Dignity of life: Moral philosophy, organizational theory, and hostage rescue-I*.

Baheretibeb, Y., Wondimagegn, D., Andermann, L., & Law, S. (2025). "Blood is thicker than Water" Experiences and perspectives of family caregivers of people living with severe mental illness at Holy Water traditional healing sites, Addis Ababa, Ethiopia. *Frontiers in Psychiatry*, *15*, Article 1495058. https://doi.org/10.3389/fpsyt.2024.1495058

Bandak, A. (2017). The social life of prayers–introduction. *Religion*, *47*(1), 1–18. https://doi.org/10.1080/0048721X.2016.1225904

Barrow, R. (2007). *An introduction to moral philosophy and moral education*. Routledge.

Brown, M. (2013). Emile Durkheim: Structural functionalism, adventure and the social order. In *Outdoor adventure and social theory* (pp. 23–33). Routledge.

Blidstein, M. (2017). *Purity, community, and ritual in early Christian literature*. Oxford University Press.

Bogaert, A. (2025). Impurity, moral substantiality, and social control: A gender perspective. *Religions*, *16*(1), Article 80. https://doi.org/10.3390/rel16010080

Boudon, R. (2017). *The origin of values: Sociology and philosophy of beliefs* (Reprint ed.). Routledge. https://doi.org/10.4324/9781315133645

Cossu, T. (2024). The pure and the impure: Anthropological approaches for the study of the ancient world. *Medea*, *10*(1), 1–15. https://ojs.unica.it/index.php/medea/article/view/6563

Douglas, M. (2002). *Purity and danger: An analysis of concepts of pollution and taboo*. Routledge.

Durkheim, E. (1995). *The elementary forms of religious life* (K. E. Fields, Trans.). Free Press. (Original work published 1912).

Duschinsky, R., Schnall, S., & Weiss, D. H. (Eds.). (2016). *Purity and danger now: New Perspectives*. Routledge.

Fardon, R. (2016). Purity as danger: ‘Purity and Danger’ revisited at fifty. In R. Duschinsky, S.
Schnall, & D. H. Weiss (Eds.), *Purity and danger now*: New perspectives (pp. 23–33). Routledge. https://doi.org/10.4324/9781315529738-7

Feder, Y. (2016). Defilement, disgust, and disease: The experiential basis of Hittite and Akkadian terms for impurity. *Journal of the American Oriental Society*, *136*(1), 99–116.

Feder, Y. (2021). *Purity and pollution in the Hebrew Bible: From embodied experience to moral metaphor*. Cambridge University Press.

Forrester, M. G. (2002). *Moral beliefs and moral theory* (Vol. 10). Springer. https://doi.org/10.1007/978-94-015-9994-8

Gray, K. etal. (2022). The problem of purity in moral Psychology. *Personality and Social Psychology Review*, *27*(3), 272–308. https://doi.org/10.1177/10888683221124741

Haidt, J. (2012). *The righteous mind*. Pantheon.

Koenig, H. G. (2012). Religion, spirituality, and health: The research and clinical implications. *ISRN Psychiatry*, *2012*, Article 278730. https://doi.org/10.5402/2012/278730

Lockett, D. (2008). *Purity and worldview in the Epistle of James*. T&T Clark.

Timmons, M. (2013). *Moral theory: An introduction* (2nd Ed.). Rowman & Littlefield.

Wandi, J. I., Afnita, N., & Hefni, H. (2021). Study of "functional structure" Emilie Durkheim Reviewed from educational anthropology on character and behavior society. *Ikhtisar*, *1*(1), 39–51.